## ኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር ባለአክሲዮኖች በሙሉ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ እጩዎችን ለመጠቆም የወጣ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር SIB/32/2012 እ.ኤ.አ፣SIB/48/2019 እ.ኤ.አ ኢንሹራንስ ቢዝነስ አዋጅ ቁጥር 746/2012 የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማና የምርጫ አፈፃፀም መመሪያ 2019 እ.ኤ.አ መሰረት የኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር ባለ አክሲዮኖች ህዳር 7 ቀን 2017 ዓ.ም ባካሄደው 16ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የቦርድ አባላት ምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት መመረጣቸው ይታወቃል።

በዚሁ መሰረት ኮሚቴው እጩዎችን ለመቀበል የሚያስችል ዝግጅቱን ያጠናቀቀ ሲሆን ኮሚቴው የዳይሬክተሮች ቦርድ እጩ አባላት ጥቆማ ከሐምሌ 13 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 13 ቀን 2018 ድረስ ብቻ ይቀበላል።

የማህበሩ ባለአክሲዮን አባላት ከላይ የተቀመጠው ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ጥቆማችሁን እንድታቀርቡ ጥሪያችንን እያቀረብን ተጠቋሚዎች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል።

1. የኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር ባለአክሲዮን መሆን አለበት፣
2. እድሜው/ዋ ከ30 ዓመት በላይ የሆነ/ች፣
3. ተጠቋሚዉ በህግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉ ተቋም ከሆነ፤ተቋሙን የሚወክለዉ የተፈጥሮ ሰዉ የሆነ፤
4. እጩ ተጠቋሚዎች የኩባንያው የዳሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ አባል ያልሆኑ፣
5. በቂ ጊዜ ያለዉ፤ ሃቀኛ፤ ታማኝ፤ ጠንቃቃ፤ትጉህ ሠራተኛ፤ መልካም ሥነ ምግባር ያለውና በኢትዮጵያ ዉስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ዉጭ ዕምነት በማጉደል፤በማጭበርበር በወንጀል ተከሶ ያልተቀጣና ጥፋተኛ ያልተባለ መሆን ይኖርበታል።
6. የነባር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመናቸው ያላበቃ፣
7. በኩባንያዉ በቦርድ አባልነት ቢያንስ ለስድስት ተከታታይ አመታት (ለሁለት የስራ ዘመን /ተርም) በቦርድ አባልነት ያገለገሉ ከሆነ ከቦርድ አባልነት ከለቀቁ ስድስት አመት የሞላቸው፣
8. የኩባንያዉ ወይም የሌላ ኢንሹራንስ ኩባንያ ተቀጣሪ ሠራተኛ ያልሆነ፤
9. በማንኛዉም የፋይናንስ ተቋም በቦርድ አባልነት በማገልገል ላይ የማይገኝ፤
10. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆኖ ለመስራት ፈቃደኛ የሆነ/ች፣

11. ቢያንስ 75 ከመቶ የሚሆኑትን የቦርድ አባላት ከታወቀ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ የትምህርት ደረጃ ሊኖራቸው የሚገባ ሲሆን ቀሪዎቹ ደግሞ ቢያንስ የሁለተኛ ደረጃ ወይም የሱን ተመጣጣኝ የሆነ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ መሆን አለባቸው፣
12. ዕጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ተጠቋሚ የትምህርት ዝግጅት በቢዝነስ ማኔጅመንት፤በኢንሹራንስ የሥራ ዘርፍ፤በፋይናንስ ፤በአካዉንቲንግ፤በማኔጅመንት፤በኢኮኖሚክስ፤በህግ፤በቢዝነስ አድሚንስትሬሽን፤በኦዲቲንግ፤በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፤በኢንቨስትመንት ማኔጅመንት እና በመሳሰሉት መስኮች አግባብነት ያለዉ እና መሰረታዊ የሙያ ዕዉቀት ያለዉ/ያላት
13. በራሱ ወይም በሚመራው ወይም ዳይሬክተር በሆነበት ድርጅት ላይ የመክሰር ክስ ያልቀረበበት/ባት ወይም የኪሳራ ውሳኔ ያልተሰጠበት/ባት፣
14. በኪሳራ ምክንያት ንብረቱ ለእዳ ማቻቻያ ያልተወሰደበት/ባት፣
15. የባንክ ብድር ባለመክፈሉ/ሏ ምክንያት ንብረቱ/ቷ በሀራጅ ያልተሸጠ፣
16. ተጠቋሚዉ በቂ ስንቅ /ገንዘብ/ሳይኖረዉ ቼክ በመስጠት ምክንያት ሂሳቡ ያልተዘጋበት/ እንዲሁም በታክስ እና ግብር ባለመክፈል ተከሶ ጥፋተኛ ያልተባለ መሆን ይኖርበታል፡፡
17. የሚመራው/የምትመራው ወይም ዳይሬክተር የሆነበት/የሆነችበት ድርጅት ከገንዘብ ተቋማት የተበደረውን ገንዘብ ባለመክፈል ብድሩ ወደ ጤናማ ያልሆነ የብድር ደረጃ ያልዞረ፣
18. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወጡ መመሪያዎች ላይ የተጠቀሱ እና ሌሎች መመዘኛዎች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

1. በተባዕታይ ጾታ የተገለጸዉ ሁሉ ለአነስታይ ጾታም ያገለግላል፡፡
2. መስፈርቱን የሚያሟሉ ሴት ዕጩዎች ይበረታታሉ፡፡
3. የመጠቆሚያ ቅጽ ስርዝ ድልዝ የሌለበትና በአግባቡ መሞላትና መፈረም አለበት፡፡
4. ጠቋሚዉ ማህበር/ድርጅት ከሆነ ደግሞ ማህተም ተደርጎበት በኩባንያዉ ዋና መ/ቤት ወይም ቅርንጫፎች በግንባር በመቅረብ የሞሉትን ቅጽ ማስረከብ ይቻላል፡፡
5. ጥቆማዉ በዉክልና የቀረበ ከሆነ ዉክልናዉ ጥቆማዉን ለማቅረብ የሚያስችል ሆኖ የዉክልና ፎቶ ኮፒዉ ከመጠቆሚያዉ ቅጽ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
6. ጠቋሚዉ ግለሰብ ወይም ማህበር/ድርጅት ከሆነ የተጠቋሚዉን ፍቃደኝነት አስቀድሞ ማረጋገጥ አለበት፡፡
7. የጥቆማ ማቅረቢያ ፎርም በኩባንያዉ ዋና መ/ቤት የኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አ.ማ 7ኛ ፎቅ የዳይሬክተሮች መሰብሰቢያ አዳራሽ ቁጥር 19 ወይም በኩባንያዉ ቅርንጫፎች ወይም በኩባንያዉ ድረ ገጽ www.eliginsurance.com ማግኘት ይቻላል፡፡

8. **ጥቆማ ከሚከተሉት በአንዱ መንገድ ሊቀርብ ይችላል፡፡**

- በኩባንያው ዋና መስሪያ ቤት መስቀል ፍላወር አካባቢ ኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አ.ማ ሆምስ ኦፍ ሚልየንስ ሕንፃ 7ኛ ፎቅ የዳይሬክተሮች መሰብሰቢያ አዳራሽ ቁጥር 19 ውስጥ በሚዘጋጀው የታሸገ ሳጥን በአካል ቀርቦ በማስገባት፣
- በመልእክት ሳጥን ቁጥር 170791 አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ ለኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አ.ማ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ ብሎ በመላክ፤
- በኢሜል አድራሻ የሞሉትን የጥቆማ ቅጽ እስካን በማድረግ ለዚሁ ተብሎ በተከፈተ ኢሜል አድራሻ info@eliginsurance.com እንዲሁም በፋክስ ቁጥር 011-5549653 መላክ ይቻላል፡፡

9. ከጥቅምት 13 ቀን 2018 ዓ.ም በኃላ የሚቀርቡ ወይም የሚደርሱ ጥቆማዎች ተቀባይነት የላቸውም መሆኑን ኮሚቴዉ ያሳስባል፡፡

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥሮች፡-** **+251-011-5549651 ወይም +251-011-5571781 መደወል ይቻላል፡፡**

**የኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር**

**የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ**